## *የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት*

## *ሰበር ሰሚ ችሎት*

የመ/ቁ. 17352

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አበዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- ዋዜማ የልብስና ሽራ ምርቶች ኃ/የተ/የግ/ማህበር

መልስ ሰጭ፡- የነገው ሰው ትምህርት አ/ማ

*ለዳኝነት ስለሚከፈል ገንዘብ - ከስነ ስርዓት ውጭ ስለሚቀርብ ክስ /የገባኝ/ - የፍትሐበሔር ሥነሥርዓት ህግ ቁጥሮች 215፣ 320/2/፣ 207፣ 211/2/*

አመልካች ከስር ፍ/ቤት በመ/ሰጭ እንዲከፍለው የጠየቀው ወለድ በመ/ሰጭ ሊከፈለው የማገባ ቢሆንም አመልካች ክሱን ሲያቀርብ ለወለድ ጥያቄው የዳኝነት ክፍያ ያልከፈለ በመሆኑ ወለድን በሚመለከት ያቀረበው ጠያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመወሰኑና ከዚህ አንፃር የቀረበውን መስቀለኛ ይገባኝ የፌዴሪል ጠቅላይ ፍ/ቤተ ውድቅ ስላደረገው የቀረበው አቤቱታ

*ው ሳ ኔ፡-* የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በጉዳዩ የወለድ ክፍያን በሚመለከት የሰጧቸው ውሳኔዎች ተሽረዋል፡፡

1. አንድ ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ የስነ ስርዓት ስህተት የፈጸመ እንደሆነ ከተከራካሪ ወገኖች ጥያቄ ሲቀርብለት ወይም በራሱ አነሳሽነት ስህተቱን ማረም አለበት፡፡
2. የስነ ስርዓት ስህተት ፈጽሞ እንደሆነ ጥያቄው ለፍ/ቤቱ ሳየቀርብ ይግባኝ ማቅረብ አይቻልም፡፡



የመ/ቁ. 17352
ሐምሌ 28 ቀን 1997 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አበዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- ዋዜማ የልብስና ሽራ ምርቶች ኃ/የተ/የግል ማኅበር
መልስ ሰጭ፡- የነገው ሰው ትምህርት አ/ማ

### <u>ፍ ር ድ</u>

የሰበር ችሎቱ በዚህ መዝገብ የቀረበለትን ጉዳይ መርምሮአል፡፡ ለጉዳዩ መነሻ የሆነው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች እንዲከፈለው የጠየቀው ወለድ በስር ተከማሽ ሊከፍል የሚገባው ቢሆንም ከሣሹ ክሱን ሲያቀርብ ከነሐሴ 16/91 ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት ጥቅምት 27 ቀን 1994 ድረስ ያለውን ወለድ አስቦ ዳኝነት ስላልከፈለበት በዚህ ጊዜ ውስጥ የቀረበውን የወለድ ሂሣብ ፊ/ቤቱ አልተቀበለውም በማለት በመወሰኑ ነው፡፡ ጉዳዩ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት መስቀለኛ ይግባኝ ቢያቀርብም ተቀባይነት ባለማግኙቱ ጉዳዩ ለሰበር ቀርቧል፡፡

ጉዳዩ ለሰበር በመቅረቡ መልስ ሰጪ መልሱን፣ አመልካች ደግሞ የመልስ መልሱን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር ማመልከቻ በተከሣሽ እንዲከፈል የተጠየቀው ብር 562,966.74 /ምስት መቶ ስልሣ ሁለት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስልሣ ስድስት ከሰባ አራት ሣንቲም/ የወለድ ሂማብ ዳኝነት አልተከፈለበትም ተብሎ መታለፉ የሕግ ስህተት መፈፀሙን ያሳያል የሚል ሲሆን መልስ ሰጪ በበኩሉ በስር ፍርድ ቤት የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ሰህተት ተፈጽሟል የሚልበትን ምክንያት ዘርዝሮ አቅርቧል፡፡ በዚህም መሠረት ለተጠየቀው ወለድ ዳኝነት ያልተከፈለበት መሆኑ፣ በሌላው ጉዳይ የተከፈለ የዳኝነት ያልተከፈለበት መሆኑ፣ በሌላው ጉዳይ የተከፈለ የዳኝነተ ሂሣብ ለወለድ ጥያቄው ይያዝልኝ ማለት የማይቻል መሆኑ፣ በሰበር በቀረበው ጥያቄ የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠው ጥቅምት 5 ቀን 97 ሲሆን በዚህም ላይ የቀረበ የሰበር አቤቱታ አለመኖሩ፣ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበበት ጉዳይ በመስቀለኛ ይግባኝነት

ቀርቦ ውድቅ የተደረገው በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይገባ በማገለጽ ተከራክሯል፡፡ የመልስ መልስም ቀርቦ ዘመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የሰበር ችሎቱ በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ አንድ ተሟጋች መክፈል የሚገባውን የዳኝነት ሂሣብ ገቢ ሳያደርግ ክርክሩ እንደቀጠለ ፍ/ቤቱ የተገነዘበ እንደሆነ መፈፀም ያለበት ሕጋዊ ሥርዓት ምንድነው? የሚለውን ጭብጥ የማያስነሣ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

የሕግ ትርጉም ወደሚያስፈልገው ዋናው ጉዳይ ከመሄዱ በፊት ፍርድ ቤቱ መልስ ሰጪ በመልሱ ላይ ያቀረባቸውን ነጥቦች ተመልክቷል፡፡

መልስ ሰጪው በስር ፍርድ ቤት የሂሣብ ይቀናነስልኝ ጥያቄ ስላልተነሣ ለሌላ ጉዳይ የተከፈለው ዳኝነት ለወለዱ ይጣጣልኝ የሚለው ጠያቄ በሰበር ሊታይ አይገባውም ብሏል፡፡ ለፍርድ ቤት የሚከፈል ዳኝነት በአጠቃላይ ከሣሽ በሚጠይቀው ዳኝነት የሚታሰብ እንጂ ለእያንዳንዷ ርዕስ እየተለየ የሚጠየቅ ባለመሆኑ ክርክሩ የሚያስኬድ አይደለም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ጉዳዩ ለፍርድ ቤት ገቢ መሆን ያለበትን ሂሣብ የሚመለከት እንጂ በሁለቱ መካከል ያለውን ጉዳይ በቀጥታ የሚመለከት ባለመሆኑ በአንዱ ወገን መነሣት አለመነሣቱ የሚያመጣው ለውጥ የለም፡፡

ከዚህ ሌላ በአመልካች የቀረበው የሰበር ማመልከቻ የመጨረሻ ውሣኔ ያልተሰጠበት መሆኑን በመጥቀስ ጥያቄው ውድቅ እንዲሆን ጠይቋል፡፡ ሆኖም ለሰበር ችሎቱ የቀረበው ጥያቄ በመስቀለኛ ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቀርቦ ተቀባይነት ያጣ መሆኑን ከፍርድ ቤቱ ማኅደር ለመገንዘብ ተለናል፡፡ ስለዚህ የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘ አይደለም ሊባል አይችልም፡፡ የአሁኑ መልስ ሰጪ ይግባኝ ጠይቄ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔ አግኝቻለሁ የሚለውም አሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበበትና ከክስ በፊት ያለውን የወለድ ሂሣብ የሚመለከት ሳይሆን ከውሣኔ በኋላ ያለውን ሂሣብ የሚመለከት መሆኑ #ተገቢው ዳኝነት ተከፍሉበት ሣይጠየቅ ወይም ወደፊት ይከፈልበት ሳይባል ክስ ከቀረበበት ጊዜ አንስቶ ዋናው ገንዘብ ተከፍሎ አለቀ ድረስ ወለድ ታስቦ ይከፈልበት በሚል መወሰኑ ትክክል ነው የምንለው አይደለም; ከሚለው መልስ ሰጪው ራሱ በመልሱ ካካተተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የውሣኔ ክፍል መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለዚህ ሁለት የተለያዩ ጥያቄዎችንና ውሣኔዎችን በማምታታት ይኸው አሁን ለሰበር የቀረበው ጉዳይ የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘ አይደለም በማለት የቀረበው ጉዳይ የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘ አይደለም በማለት የቀረበው አስተያየት ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ወደዋናው ጉዳይ ስንመለስ ይህ ችሎት የሕግ ትርጉም ያስፈልገዋል ብሎ የያዘው የሕግ ነጥብ የዳኝነት መክፈል የነበረበት ባለጉዳይ ሂሣቡን እንዳልከፈለ ፍ/ቤቱ ሲረጋገጥ ሊሰጥ የሚገባው ውሣኔ ምንድነው? የሚለው ነው፡፡ አሁን በቀረበልን ጉዳይ



የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች የጠየቀው የወለድ ሂሣብ ለአመልካች መከፈል ያለበት ስለመሆኑ በፍርዱ ተቀብዘለአል፡፡ ፍርድ ቤቱ ከነሐሴ 16/91 እስከ ጥቅምት 27/1994 ድረስ ያለውን የወለድ ሂሣብ ብር 562,966.74 ውድቅ ያደረገው ከሣሹ ወለድ አስበው ዳኝነት አልከፈሉበትም በማለት ነው፡፡

ማንኛውም ለፍርድ ቤት ክስ የሚያቀርብ ሰው በሕጉ በተተመነው መሠረት የዳኝነት መክፈል እንዳለበት በሥነሥርዓት ሕጉ ቁጥር 215/1/ የተመለከተ ነው፡፡ በመሆኑም ማንኛውም ጉዳይ ሕጉ በሚያዘው መሠረት ከመቀጠሉ በፊት የሚመለከተው የፍርድ ቤቱ ክፍል ይህ አስተዳደራዊ የሆነ ተግባር መከናወኑን ማረጋገጥ ይጠበቀበታል፡፡ በሌላ በኩል በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት በሕጉ መሠረት የዳኘነት መከፈል የነበረበት ተከራካሪ ወገን ይህን ተግባር ሳይፈጽም ቢቀር ሕጉ ያስቀመጠው መፍትሄ ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡

የሥነ ሥርዓት ሕጉ በሙግት ሂደት የሚፈፀሙ ጉድለቶችን ለማረም የተለያዩ መፍትሄዎችን አስቀምጧል፡፡ በዋናነትና በተለምዶ በብዛት ሥራ ላይ የሚውለው ጉዳዮችን ለይግባኝ ፍ/ቤት እያቀረቡ ስህተቶች እንዲታረሙ መጠየቅ ነው፡፡ ይህ የመፍትሄ አቅጣጫ አንድ በሙግት ሂደት የተፈፀመን ስህተት ስህተቱን ፈፀመ ለተባለው ፍርድ ቤት ሳይሆን በእርከን የበላዩ ለሆነው ሌላ ፍርድ ቤት በማቅረብ የሚከናወን ሲሆን በሥነሥርዓት ሕግ ቁ. 320 እና ተከታዮቹ ቁጥሮች መሠረት የሚሰተናገድ ነው፡፡

በሙግት ሂደት የሚከሰቱ ስህተቶችን ለማረም ግን ይግባኝ አንዱ ምናልባትም የመጨረሻው አማራጭ እንጂ ብቸኛው አማራጭ አለመሆኑን ከሕጉ አደረጃጀት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ የሥነሥርዓት ሕግ ስህተቶችን ወደ የግባኝ ፍርድ ቤት መውሰድ ብቻ ሳይሆን ጉዳዩን ስህተቱን ፈፀመ ለተባለው ፍርድ ቤት ማቅረብ የሚቻልበትን ሥርዓት አስቀምጡል፡፡ ከፍትሀብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁ.320/2/ መገንዘብ እንደሚቻለው አንድ ፍርድ ቤት የገዛ ትዕዛዙን ለማሻሻል፣ ለማረም ወይም እንደገና ለማጣራት በሕግ ሥልጣን የተሰጠው ከሆነ ይግባኝ ማቅረብ የሚቻለው ይኸው ቅድመ ሁኔታ ከተሟላ ብቻ መሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡ አግባብነት ያለው የሕጉ ክፍል እንዲህ ይላል በተሰጠው ፍርድ ወይም ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ ለማለት የሚቻል ቢሆንም እንኳ ፍርድ ወይም ትዕዛዝ የሰጠው ፍርድ ቤት በዚህ ህግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ፍርዱን ለማረም ለማሻሻል ወይም እንደገና ለማጣራት የማችል ከሆነ ይኸው ሥርዓት አስቀድሞ ሳይፈፀም ይገባኙን ማቅረብ አይፈቀድም፡፡

ይህ ድንጋጌ አንድ ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ ወይም ፍርድ ራሱ መልሶ የሚያይበት ሥርዓት መኖሩንና ቀዳሚው የመፍትሄ አቅጣጫ ማንኛውንም ጉዳይ ወደ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት መውሰድ ሳይሆን ጉዳዩን ለያዘው ፍርድ ቤት ለራሱ በማቅረብ

ተሠራ የተባለው ስህተት እንዲታረም መጠየቅ መሆኑን በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ ይህ አሠራር የይግባኝ ፍርድ ቤቶችን መጨናነቅ የሚቀንስ ከመሆኑ ባሻገር ተከራካሪ ወገኖች በአቅራቢያቸው ላለውና ጉዳዩን ለሚያውቀው ፍርድ ቤት ጥያቄያቸውን አቅርበው የተቀላጠፈ መፍትሄ የሚያገኙበትን ሁኔታ የሚያመቻች፣ ጉዳዮች ባነሳ ጊዜና ወጪ እንዲስተናገዱ ዕድል የሚሰጥ አሠራር ነው፡፡

በሥነሥርዓት ሕጉ መሠረት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው ፍርድ ቤት በዚህ ሁኔታ መልሶ ቀድሞ ያያቸውን ጉዳዮች የሚያስተናግድባቸው በርካታ መንገዶች ቢኖሩም /ለምሣሌ አንቀጽ 6፣ 74፣ 78፣ 358/ አሁን ከቀረበልን ጉዳይ ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነትና ተፈጻሚነት ያለው ግን በሥነሥርዓት ህጉ አንቀጽ 207 ላይ የሠፈረው መሠረተ ሃሣብ ነው፡፡ የዚሁ ሕግ ሙሉ ክፍል የሚከተለው ነው፡፡

በህግ ተለይቶ ካልተደነገገ ወይም ፍርድ ቤቱ በሌላ አኳኋን እንዲፈፀም ልዩ ተዕዛዝ ካልሰጠ በቀር በዚህ ሕግ የተመለከቱትን ውሣኔዎች ወይም በውሣኔዎቹ መሠረት የሚወጣውን ደንብ ባለመፈፀም ከሥነሥርዓት ውጭ የሆነ ክስ ሲቀርብ ወይም በክሱ ውስጥ ደንብ ውጭ የሆኑ ተግባር ሲፈፀም፣ ከተከራካሪዎቹ ወገኖች አንዱ ባመለከተ ጊዜ ወይም ፍርድ ቤቱ በራሱ ሥልጣን ይህ ከሥነሥርዓት ውጪ የቀረበው ክስ በከፊል ወይም በሙሉ እንዲሠረዝ ወይም ክሱ ተሻሽሎ እንዲቀርብ በዚህም ምክንያት ስለሚደርሰው ኪሣራና ስለሌላውም ወጭ ተስማሚ መስሎ የታየውን ትዕዛዝ ይሠጣል፡፡

የዚሁ ሕግ የእንግሊዝኛ ቅጂ እንዲህ ይነበባል፡፡

207 <u>Principle</u>

Unless otherwise expressly provided by law of directed by the court, where irregularities arise from noncompliance with any provision of this code or regulation made there under the court, many of its own motion or on the application of either party, set aside such proceedings either party, set aside such proceedings either wholly or in part as irregular, or amend them or make, on such term as it thinks fit, such other order as may be appropriate.

ከዚሁ የሥነ ሥርዓት ህግ መንደርደሪያ መርህ መረዳት እንደሚቻለው በማንኛውም ፍ/ቤት በሚካሄድ ክርክር ሥነሥርዓቱን ያልተከተለ ክስ የቀረበ እንደሆነ ወይም በክሱ ሂደት ሕጉ ያስቀመጣቸው የሥነሥርዓት ደንቦች በአግባቡ ያልተፈፀሙ እንደሆነ ፍርድ ቤት ሥርዓቱ ከሚያዘው ውጪ የተሠራውን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ሊሰረዝ ይችላል፡፡ ይህም የሚከሃወነው በተከራካሪዎች አመልካችነት ብቻ ሳይሆን በፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነትም ጭምር ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ መርህና



ደንብ መሠረት በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ ዳኞች በሚያካሂዱት የዳኝነት ሥራ የሥነሥርዓቱን ደንብ ያልተከተለ ክንውን በራሳቸውም ሆነ በአስተዳደር ክፍሉ መፈፀሙን ሲያውቁ ወይም ሲደርሱበት ስህተቱን እንዲያርሙ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በፍርድ ቤቶች አካባቢ የሚታየው የተለመደው አሠራር ዳኛ የሰጠውን ትዕዛዝ መቀየር አይችልም፣ መቀየር የሚችለው የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ብቻ ነው የሚል ቢሆንም ይህ በተለምዶ የዳበረው አሠራር የሥነሥርዓቱ ሕጉ ያስፈረደውን ከላይ የተጠቀሰውን መሠረታዊ መርህ የሚጻረር ነው፡፡ ሥነ ሠርዓት ነክ የሆነን ጉዳይ የሚመለከት እስከሆነ ድረስ ባለጉዳዮች ወደ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት መሄድ ሳያስፈልጋቸው ስህተቱን ለፈፀመው ፍርድ ቤት ማመልከት ይፈቀድላቸዋል፣ ዳኞችም እርግጥም ስህተት መሠራቱን ካመኑበት ስህተቱን የማረም ሥልጣንም አላቸው፡፡ /የሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁ.209/

ወደያዝነው ዋናው ጭብጥ ስንመለስ የከፍተኛ ፍ/ቤት ወለድን አስመልክቶ የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው ወለድ ሊከፈለው አይገባም በሚል ምክንያት ሳየሆን ለፍርድ ቤት ገቢ መሆን የነበረበትን የዳኝነት ሂሣብ አልከፈለም በማለት ነው፡፡ በሥነሥርዓት ሕጉ ቁጥር 215/1/ እንደተደነገገው ለፍርድ ቤት የሚቀርቡ ክሶች ሁሉ ዳኝነት ካልተከፈለባቸው በቀር ተቀባይነት አያገኙም፡፡ ስለዚህ የዳኝነት ሂማብ ለፍርድ ቤት ገቢ ማድረግ በክስ ሂደት መከናወን ያለበት ተግባር ነው፡፡ የዳኝነት ክፍያ መጠናቀቅ ያለበት ክሱ ሲቀርብ እንደሆነ ከድነጋጌው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም ይህን ሥራ እንዲያከናውኑ የተመደቡ የሚመለከታቸው የፍርድ ቤቱ ክፍሎች ይህ ህጉ የሚጠይቀውን ሥርዓት መከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ማከናወን ያለበት ይህ ተግባር ሳይከናወን ቀርቶ ክሱ ለፍርድ ቤት /ለዳኛ/ ቢቀርብ ክሱ ከሥነ ሥርዓት ውጪ የቀረበ /procedurally irregular/ ይሆናል፡፡ በፍትሐብሄር ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 207 እንደተደነገገው የሥነሥርዓት ሕጉን ወይም በሱ መሠረት የሚወጡ ደንቦችን በመጣስ የቀረበን ከሥነሥርዓት ውጪ የተፈፀመን ተግባር የማቃናት ሃላፊነት ለፍ/ቤቱ የተሰጠ በመሆኑ የሥነሥርዓት ግድፈት የተፈፀመ መሆኑ ሲታወቅ በዚህ መሠረት መከናወን ይኖርበታል፡፡ በዚህ መሠረት ያልተከፈለ የዳኝነት ክፍያ ካለ የክሱን ሂደት አስመልክቶ የተፈፀመ የሥነ ሥርዓት ግድፈት መኖሩን ስለሚያመለክት ዳኞች በተጠቀሰው ሕግ መሠረት ግድፈቱን በማስተካከል ያልተከፈለ ሂሣብ ካለ ተሰልቶ እንዲከፈል ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በያዝነውም ጉዳይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማድረግ የነበረበት ይህንን ነው፡፡ አመልካች ወለድ እንዲከፈለው ጠይቋል፡፡ ይኸው የአመልካች ጥያቄ በሕግ ተቀባይነት ያለው መሆኑንም ፍ/ቤቱ ተቀብሎታል፡፡ በመሆኑም ያልተከፈለ ሂሣብ ካለ በሥነሥርዓት ሕጉ ቁጥር 207 መሠረት ማስከፈል ሲገባው ይህን አልፎ የቀረበውን

ክስ በዚህ ምክንያት ውድቅ ማድረጉ ሕጉ ያስቀመጠውን የሙግት አመራር የተከተለ አይደለም፡፡ በመሆኑም ይህ ፍርድ ቤት አልተቀበለውም፡፡

የፍተሀብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 211/2/ #ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ በተባለበት ጉዳይ ላይ የተፈፀመውን ማንኛውንም የሥነ ሥርዓት ጉድለት በራሱ አስተያየት ሊያርም ይችላል; በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚህም መሠረት የሰበር ችሎት የዳኝነትን አከፋፈል አስመልክቶ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፈፀመውን የሥነ ሥርዓት ጉድለት ማቃናት እንዳለበት አምኖአል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች ከ16/12/91 እስከ ጥቅምት 27/1994 ዓ.ም ያለውን የወለድ ክፍያ በሚመለከት በመዝገብ ቁ.11641 የሰጠውን ውሣኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 15574 የሰጠውን ውሣኔ ሽሯል፡፡
2. መልስ ሰጪ ከ16/12/91 እስከ 27/2/94 ላለው ጊዜ በዋናው ገንዘብ ላይ 9% ወለድ ይከፈል፡፡
3. በዚሁ በተፈረደው የወለድ መጠን ያልተከፈለ የዳኝነት ገንዘብ አመልካቹ ለጠቅላይ ፍ/ቤቱ ገቢ ያድርግ፡፡ የውሣኔው ገልባጭ የሚሰጠው የዳኝነቱን ገንዘብ ገቢ ማድረጉ ከተረጋገጠ በኋላ ነው ተብሏል፡፡
4. መልስ ሰጪ በዚህ ፍርድ ቤት ውሣኔ አመልካች ለዚህ ፍርድ ቤት ገቢ ያደረገውን የዳኝነት ሂሣብ ይተካለት፣ ሌላው በዚህ ፍርድ ቤት ያለውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሣኔያቸው ላይ ለውጥ መደረጉን እንዲያውቁት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና ለጠቅላይ ፍ/ቤት የዚህ ውሣኔ ግልባጭ ይላክ፡፡



## የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
## ሰበር ሰሚ ችሎት

የመ/ቁ. 14605

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አበዱልቃድር መሐመድ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ
ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት

መልስ ሰጪዎች፡- 1. ኮሜት ትራንስዓርት ድርጅት
2. ሸበሌ ትራንስፖርት ድርጅት
3. በከልቻ ትራንስፖርት ድርጅት
4. ወይራ ትራንስፖርት ድርጅት
5. አዲስ ሜካኒካል ድርጅት
6. አቶ ዮሐንስ ተሰፋ

*ስለ ማጓጓዝ ስራ - የአጓዡ ኃላፊነት - የተመዘገቡ ጓዞች ወይም ዕቃዎች የጠፉ ወይም ጉዳት የደረሰባቸው ሲሆን - በተለያዩ ምክንያቶች ከኃላፊነት መዳን የንግድ ህግ ቁጥሮች 590፣ 591፣ ውል - ውልን ስላለመፈጸም- ከዐቅም በላይ የሆነ ነይል - የፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 1792*

አመልካች በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ ከ1ኛ-5ኛ በተጠቀሱት ተጠሪዎች መኪና አቅራቢነት ነጭ ጋዝ ናፍታ አስጭኖ ከአሰብ ወደ ባህር ዳር በሚጓጓዝበት ወቅት መኪናው ተገልብጦ ዋጋው ብር 51,089.78 /ሃምሳ አንድ ሺህ ሰማንያ ዘጠኝ ብር ከሰባ ሰምንት ሳንቲም/ የሆነ ነዳጅ ስለፈሰሰ ይህንኑ ዋጋ ብር 51,089.78 /ሃምሳ አንድ ሺህ ሰማንያ ዘጠኝ ብር ከሰባ ሰምንት ሳንቲም/ ከ1-5 ያሉት ተጠሪዎ እንዲሁም የመኪናው ባለንብረት 6ኛ ተጠሪ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉት ያቀረበውን ጥያቄ ፍ/ቤቱ ነዳጁ